# ግጭት አስወጋጅ ወይስ ህቡዕ የሁከት አዘጋጅ?

**/ክፍል ሁለት/**

ሐሰን አባፊጣ

ውድ አንባቢዎቼ በክፍል አንድ ፅሑፌ ላይ ራሱን ዓለም አቀፍ የግጭት አስወጋጅ ቡድን እያለ የሚጠራውና ማረጋገጫ የሌላቸውን ትርኪ ምርኪ ወሬዎችን እየቃረመ በሀገራችን ላይ ውንጀላ የሚነዛውን ድርጅት ለማሳየት ሞክሬያለሁ። ቀጣዩ ምልከታዬ ደግሞ እነሆ።…

… የኒዩ ሊበራል ቡድኑ ያልተረዳው ብዙ ነገር አለ፡፡ ኢትዮጵያዊነት አልገባውም፡፡ አሊያም ለፖለቲካ ንግዱ ጀማሪ አስመስሎታል ማለት ይቻላል፡፡ እናም ኢትዩጵያዊያን ዛሬ የምንገኝበት ወቅት በተራ ወሬና አሉባልታ የምንፈታበት አለመሆኑን "ተቋሙ" መገንዘብ ያለበት ይመስለኛል፡፡

እስቲ ሌላኛውን የቡድኑን አሉባልታ ላስከትል፡፡ መንግስት የጋዜጠኞችን ሃሳብ በነጻነት የመግለጽ መብት መገደቡን ያትታል፡፡ "የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ ነው" እንዲሉት ዓይነት መሆኑ ነው አባባሉ፡፡ እርግጥ ቡድኑ መሰል ወንጀላዎችን ለዓመታት ቢሰልቅ መቆየቱ የታወሳል፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ ህገ - መንግስቱና ህገ - መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ ሁለት ቆብ አጥልቀው በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ በተጨባጭ የተያዙ 'ጋዜጠኞች' እና የግብረ- ሽበራ አካላት በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡

ለነገሩ ከስያሜው ጋር የማይገናኘው ቡድን ጥያቄው "ህገ - ወጦችና የጥፋት ኃይሎች ለምን ለቅጣት ቀረቡ?" የሚል ከሆነ አስቸጋሪ ጉዳይ ነው፡፡ ሁላችንም እንደምንረዳው የምንኖረው ህግና ስርዓት በሰፈነበት ሀገር ውስጥ ነው፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ህዝብ ለማተረማመስ መንቀሳቀስ በህግ ማስጠየቁ አይቀሬ ነው፡፡ እናም መንግስት በሽብር ተግባራት የተሰማሩ የሚዲያ አባላትን ከህግ ፊት ቅረቡ ማለቱ ግዴታው ነው፡፡ ዜጎችን ከእልቂት የመታደግ ኃላፊነት አለበትና፡፡

ጋዜጠኛ ተብዬዎችም ይሁኑ አጫፋሪዎቻቸው ለጥፋታቸው በአደባባይ ይቅርታ የጠየቁበት ሁኔታ እያለ፤ ቡድኑ ለወንጀለኞች ወግኖና ወገቡን ታጥቆ ለክርክር መቅረቡ አንድ ለዓለም ህዝብ ደህንነት እተጋለሁ ከሚል ተቋም የሚጠበቅ አይመስለኝም– ምናልባትም በግርግር ስልጣንን ከሚቋምጡ የጥፋት ኃይሎች ጋር ማህበርተኛ በመሆን የሚገኝ ጥቅም ካለ አብሮ ለመቀራመት እንጂ፡፡ እናም ህግና ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት ወንጀለኞች ለህግ መቅረባቸው አግባብ ብቻ ሳይሆን፤ ግድም ነውና መንግስት ሃሳብን በነጻነት በመግለጽ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ገብቷል መባሉ ፍጹም ከእውነት የራቀ ነው፡፡

በሀገሪቱ የተለያዩ ሃይማኖቶች መኖር ለሀገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት የራሱን ሚና እየተጫወተም መሆኑን አትቷል – ቡድኑ፡፡ በመሰረቱ ብዝሃነት በራሱ እንከን አደለም፡፡ ብዝሃነትን በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል አውድ በሰፈነበት ሁኔታ በእምነት፣ በቋንቋም ይሁን በብሔር መለያየት አሉታዊ ገጽታ ሊኖረው አይችልም፡፡

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተፈቃቅደው የኖሩባትና እየኖሩባት ያለች ሀገር ነች፡፡ ይሁን እንጂ ልዩነቶቻቸውን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሊያስተናግድ የሚችል መንግስት ተፈጥሮ አያውቅም፡፡ ያም ቢሆን ግን ኢትዮጵያዊያንን ለአለመረጋጋትና ለእር በርስ መተላለቅ ዳርጓቸው አያውቅም፡፡ ኢትዮጵያዊያን በሃይማኖት ልዩነት ወደ አልተፈለገ ፍጥጫ መግባት ከነበረባቸው ዘንድሮ ሳይሆን ድሮ ነበር፡፡ ያ ዘመን ዛሬ አክትሟል፡፡ እናም የሃይማኖት ልዩነቶቻችን ችግሮቻችን አደሉም፡፡

ዓለም አቀፍ የግጭት አስወጋጅ ቡድን በርእሱ ግምት ለኢትዮጵያ የሚበጀውን 'መላ' ስንዝሯል– "ድንቄም መላ" አሉ አባባ ሞላ። ያም ሆነ ይህ ቡድኑ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች እንዲጠናከሩና እንዲታገዙ ትዕዛዝ ቢጤ ይሁን አስተያዬት ባይገባኝም የተሰማውን ሰብኳል፡፡ ለነገሩ የተቃዋሚዎች መኖር የሚፈለግ እንጂ የሚገፋ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ግጭት አስወጋጅ ነኝ ባይ ቡድኑ ቢልም፣ ባይልም፡፡ ማንም ቢፈልግም፣ባይፈልግም የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖር የግድ ነው፡፡ ህገ - መንግሥታዊ ዋስትና አለውና፡፡

ይሁን እንጂ በተጨባጭ እንደምናስተውለው የረባ ፖለቲካ ቡድኖች አሊያም ተቃዋሚ ፓርቲዎች አልተፈጠሩም፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ህዝቡን "እናውቅልሃለን" ብለው ብቅ የሚሉ ፖለቲከኞቻችን አይደለም ሀገርን ራሳቸውንም ማስተዳደር የተሳናቸው የመንደር ጉልበተኞች ዓይነት ናቸው፡፡

እነዚህ ወገኖች ህገ - መንግስቱን በኃይል ንደው ቤተ መንግስት መግባትን እንጂ የነጠረና የበቃ የፖለቲካ መስመር አንግበው ኢትዮጵያዊያንን ማማለል አልቻሉም፡፡ ይልቁንም በምግባራቸው በህዝቡ እየተጠሉ ከጨዋታ ውጭ እየሆኑ ነው፡፡ ዛሬ ቡድኑ ጠበቃ ልሁንላችሁ የሚላቸው የባህር ማዶዎቹ 'ፖለቲካኞቻችንም' በምግባራቸው ከጨዋታ ሜዳው የወጡ መሆናቸው አይዘነጋም፡፡

የፖለቲካ ምህዳሩ በመጥበቡ ሁኔታዎች አልተመቻቹምና መክሰማቸው አስግቶኛል እያለ የሚሟገትላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን አጥር ቆም ጥግ ቆሞ ድንጋይ እንደሚወራወር ፈሪ ልጅ ባህር ማዶ ተሻግረው ርስ በርሳችን ሊያባሉን ከመሯሯጥ በስተቀር አንዳችም ሊያጓጓ የሚችል የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘው መቅረብ የተሳናቸው፤ የማይችሉም ናቸው፡፡ በተቃራኒውም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በብሔርና በቋንቋ ስም በመነገድ ሊያተራምሱን የሚሯሯጡና ከፀረ - ኢትዮጵያዊያን ጎን ተሰልፈው ሀገራችንን ለማፍረስ የሚቋምጡ ህልመኞች ናቸው– የበግ ለምድ ለብሰው ሊቀላቀሉን የሚዳዳቸው የዘመን ቀበሮዎች፡፡ ይህ ተጨባጭ ሃቅ ነው፡፡

ግጭቶችን በማስወገድ ላ እሰራለሁ የሚለው ቡድን ታዲያ የሚከራከረው ለዚህ ዓይነቱ የጥፋት ኃይል መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ስኬታማ ጥፋተኞች አለመሆናቸው ቆጭቶታል፡፡ ምክንያቱም መሰል ጥፋቶችን ካላስመዘገበ የጥፋት ዘመቻውን የሚያጧጡፉበት የሥራ ማስኬጃ አሊያም የውሎ አበል ስለማይከፈለው ነው፡፡

ከሁሉም በላይ እኔን የገረመኝንና ያሳፈረኝን ነጥብ ላስከትል፡፡ ይኸውም አቶ መለስ በሌሉበት ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ለአደጋ የተጋለጠ እንደሚሆን ቡድኑ ማሚረቱ ነው፡፡ ማንም በግልፅ እንደሚያውቀው የአቶ መለስ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር ፡፡ ብልሁ መሪያችን እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ አመራር የተጫወቱት ሚና የበዛ ነው፡፡ ይህንን ማንም መካድ አይቻለውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኢህአዴግን ከግለሰቦች ጋር ህልውናው አብሮ የሚያከትም ተራ ድርጅት አድርጎ መሳል ካለማወቅ የመነጨ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ አቶ መለስን የፈጠረው ኢህአዴግ አደለምን? እናም የመለስ አለመኖር ምንም ጉዳት አይኖረውም ባይባልም፣ የሀገርን አለመረጋጋት ያስከትላል መባሉ ግን ከአጉል ቅዠት የዘለለ ሊሆን አይችልም፡፡

ቡድኑ ልቦና በማጣቱ ነገሩን አውቆ ከስር መሰረቱ ለማወቅ ባለመፈለጉ እንጂ ኢህአዴግ ሚሊዬን መለሶችን ማፍራት የቻለ ታላቅ ድርጅት ነው፡፡ መለስ ሰው ናቸውና እንደሚያልፉ ስለሚያውቁ ራሳቸውን ተክተዋል፡፡ የመለስን ሞት ተከትሎ ሁሉም ነገር በነበረበት መቀጠሉም ኢህአዴግ የቤት ስራውን ጠንቅቆ እንደሰራ ያመላክታል፡፡

እርግጥ ቡድኑ የመለስን የፖለቲከኝነት አማተሪዝም አቀንቅኗል፡፡ መቼም አታሚርት አይባልም፡፡ የቡድኑ የተሳሳተ ግምት የመነጨው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በታሪካችን ታይቶም ሆነ ተሰምቶም ስለማይታወቅ ደንግጦ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የተሳሳተ ግምት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ዘንድሮ ድሮ አይደለም– አዲስ የህዳሴ ዘመን እንጂ፡፡ ወጣም ወረደ የሆነውና የሚሆነው ለሠላም ቆሜያለሁ የሚለው ዓለም አቀፍ ግጭት አስወጋጅ ቡድን ከሚገምተውና ከሚመኘው ፍጹም ይቃረናል፡፡ ሁሉም ነገር ህግና ሥርዓት ስለተበጀለት የመለስ ሞት አለመረጋጋትን አላስከተለም፡፡ ኮሽ ባለ ቁጥር የሚበረግግ ትውልድና መንግስት የሚኖሩበት ዘመን ተረት በመሆኑ የቡድኑ ሟርት እንደ ጉም ብን ብሎ ከስሟል፡፡…

ያም ሆነ ይህ ግን እኔ አስገራሚውን የቡድኑን ሪፖረት ትዝብቴን ቀጥያለሁ፡፡ ቀጣዩ የቡድኑ አሉባልታ ተከታዩ ነው፡፡ ከ1990 — 1992 ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ባደረገችው ጦርነት ኢትዮጵያዊያን ተገደው እንደዘመቱ አድርጎ ጽፏል፡፡ "ጉድ በል ጎንደር" ማለት ይኼኔ ይመስለኛል፡፡…

እኔ የነቃሁ የበቃሁ የታሪክ ምሁር ባልሆንም፣ ኢትዮጵያዊያን በሉዓላዊነታችን የተደራደርንበትና ድንበራችንን ለማስከበር ያቅማማንበት ጊዜን አላስታውስም፡፡… የትኛውም ዶሴ ቢገለጥ፣ የቱንም ያህል የታሪክ ድርሳናት ቢገላበጡ እምቢ ለነጻነት ባይነታችንን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፡፡ ሻዕቢያን ሆ! ብሎ ወጥቶ አይቀጡ ቅጣት የቀጣውም ያው የባለ ታሪኮቹ የአበውና እመው ልጅና የልጅ ልጅ ነው። ኢትዮጵያ ሃገሩን ከጠላት ለመጠበቅ ተገዶ ዘመቻ ዘመተ ቢባል እውነትም ያስተዛዝባል ፣ ያሳፍራልም፡፡

የምር ምን ዓይነቱ ዓይኑን በጨው የታጠበ አሉባልተኛ ቡድን ነው ጃል፡፡ ሃቅን መካድ እውነትን መደፍጠጥ የህሊናም፣ የታሪክም ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ የቡድኑ ግልብ ትችት እኔን መሰል ተራ ዜጋን እንኳን ሊያሳምን አቅም ያጣ አቅመ ቢስ ውንጀላ ነው፡፡

“ትችቶችን መሰንዘር በአሸባሪነት ያስጠረጥራል” ይላል– ሌላኛው የቡድኑ የማደናገሪያና የዓለም ህብረተሰብ የማወናበጃ ስልቱ። እርግጥ የሚወናበድለት የሚኖር አይመስለኝም፡፡ የግብረ ሽበራ ሴራ ገፈት ቀማሿ ኢትዮጵያ ሽብርንና አሸባሪነትን እንደማትታገስ ግልጽ ነው፡፡ በተጨባጭም ሀገርንና ህዝብን ለማሸበር የዜጎችን ህይወት ለመቅጠፍ፣ አልፎ ተርፎም ስርዓቱን በኃይል ለመናድ በተግባር ሲንቀሳቀሱ እጅ ከፈንጅ የተያዙ ፀረ -ሰላም ሃይሎችን በቁጥጥር ስር አውላለች፡፡ ይህ ህግና ስርዓትን የማስፈን ጉዳይ እንጂ ዜጎችን በአሸባሪነት የመፈረጅ ጉዳይ አይደለም– እኔ እስኪመገባኝ ድረስ፡፡

ትክክለኛ ርምጃም ይመስለኛል፡፡ መንግስት ስርዓት የማስጠበቅ ግዴታም እንዳለበት መዘንጋት የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ ቡድኑ እንደሚያራግበው ጥፋተኞች በቁጥጥር ስር የዋሉት በማን አለብኝነትና በከንቱ ጥርጣሬ ሳይሆን በተጨባጭ አስረጂዎች ነው፡፡

የቡድኑ ክስ ወጥነት የሚጎድለውና እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው፡፡ በአንድ በኩል የመለስ ፖሊሲዎች ሀገሪቱን ከሌላው ዓለም እንደነጠላት ይሰብካል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገሪቱ ኢንቨስትመንት በመሳብ ላይ መሆኗን ይመሰክራል፡፡ “በአንድ አፍ ሁለት ምላስ” ይሏል እንዲህ ነው፡፡ የሆኖ ሆኖ ቡድኑ አውቆም ይሁን ሳያውቅ በጎ ገፅታችንን መስክሯል፡፡ እውነታውን ከእኛ ከኢትዮጵያን የበለጠ የሚያውቅና መመስከር ያለበት ባይኖርም፤ ተቋሙ የተምታታ ፍሬ ፈርስኪ ዲስኩሩን አሰራጭቷል፡፡

ግን ፖርቱን እንዳነበበ ዜጋ ጥያቄ አለኝ፡፡ ይኸውም ‘የዓለም ህብረተሰብ በአንድ ድምጽ ያሞገሰውን ሁለንተናዊ ገጽታችንን  ቡድኑ ለማጠልሸት ታጥቆና ክንዱን ሰብስቦ የመነሳቱ ምክንያት ምንድን ነው?’ የሚል ነው፡፡ ድፍን ዓለም የተቀበለውን አዎንታዊ ገጽታችን ለቡድኑ ለምን አልገለጥልህ  እንዳለው አልገባኝም፡፡

የዓለም ህዝብ ማዬትና መስማት የተሳነው መሆኑን ሃቅን የማይናገር አድርጎ መቁጠሩ ካልሆነ በስተቀር ቡድኑ ራሱ ማን አለብኝ ባይ ነው፡፡ የዓለምን ህዝብና ኢትዮጵያዊያንን ንቀት ይመስለኛል - እርግጥም ሀገራችንን በደፈናው ለማጥላላት የተሰለፈ ደፋር ተቋም ነው፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የኢንቨስትመንትን ፍሰት መሳብ መቻልና የዓለም ህብተሰብን ይሁንታ ማግኘት የተቻለው ዝም ተብሎ አይደለም – የቤት ስራችንን አጥብቀን ስለ ሰራን እንጂ፡፡ ሰላም፣ መረጋጋትና ምቹ የስራ ድባብ በመፍጠራችን እንጂ፡፡…

አሁንም የቡድኑን ከንቱ ወንጀላዎች በመምዘዝ መታዘቤን ቀጥያለሁ፡፡ ተከታዩ ትዝብቱ የወሰደኝ በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት ወደሌለው የሞኝ ክስ ነው፡፡ መንግስት ሃይማኖትን በኃይል እየደፈጠጠ መሆኑን ጽፏል– ቡድኑ መንግስት የእስልምና ሃይማኖትን በኃይል እንደተጫነም ሰብኳል፡፡

ይኼ ፍጹም ከእውነት የራቀ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው፡፡ ምክንያቱም መንግስትና ሃይማኖት ሁለት የተለያዩ ክንፎች በመሆናቸው መንግስት በሃይማኖት ተቋማት ላይ ጣልቃ ለመግባት ፍላጎቱም መብቱም የለውም፡፡ ህገ - መንግስቱም አይፈቅድለትም፡፡ በህገ - መንግስቱ በግልጽ እንደተደነገገው አንደኛው በሌላኛው ጣልቃ የሚገባበት  ምንም ምክንያት የለም፡፡

ይሁን እንጂ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት ሀገር በእምነት ሽፋን ሲፈርስ ህዝቡን የሚያበጣብጥ እንከን ሲፈጠር እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሁላችንም እንደምናስታውሰው መንግስት ሀገሪቱን ለማሸበርና ነባሩን ብዙሃን ሙስሊም ለመበታተን ሲሯሯጡ በነበሩ እጅግ ጥቂት “ሃይማኖታዊ ነጋዴዎች” ከድርጊታቸው ለማረም የሚጠበቅበትን እርምጃ ወስዷል፡፡ ዜጎችን ከአደጋ የመጠበቅ ሀገርን ከሽብር መታደግ ግዴታውም ኃላፊነቱም በመሆኑ እርምጃው የሚያስወቅሰው አይደለም፡፡ ተግባሩ ህግና ስርዓትን ማስከበር ነውና።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ጉዳይ አለ። ይኸውም እስልምናም ይሁን ሌሎች እምነቶች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ህገ - መንግስሥታዊ ዋስትናቸው መረጋገጡ ነው፡፡ ቡድኑ ታፈኑ እያለ በስማቸው ለማትረፍ የሚወተውተው ሙስሊሞች እንዳልተበደሉ ዘንግቶት አደለም፡፡ እውነት እንነጋገር ከተባለ እስልምና የተበደለበት ዘመን አክትሟል፡፡ እስልምና ታፍኖ የኖረው ኢትዮጵያ የአንድ ሃይማኖትና የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ምድር ተደርጋ በምትቆጠርበት በዚያ በጨለማው ዘመን ነበር፡፡

እናም በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ስም ለነገድ የቃጣው በህዝብ ሙስሊሙና በመንግስት የተቀናጀ ጥረት የተወገደው አክራሪ ኃይል ፖለቲካዊ ግብ ያለው እንደነበር ግንዛቤ መያዝ ያለበት ይመስለኛል፡፡ ግጭት አስወጋጅ ነኝ የሚለው ቡድኑ ኢትዮጵያን ለትርምስ አጭቷት በመሆኑ እንጂ የመንግስትና የሙስሊሙን ሠላም ወዳጅነት ማውገዝ ባልተገባው ነበር፡፡ ይህን እኩይ ተግባር ማክሸፍና ሀገሪቱን የማረጋጋት ሥራ ደግሞ በዋነኛነት የሙስሊሙ ህብረተሰብ ቢሆንም፤ መንግስትም ድርሻ አለውና ያልተገባ የውንጀላ ታርጋ ሊለጠፍበት አይገባም፡፡

ከሁሉም በላይ የሚገርመው ግን ግጭትን አስወግዳለሁ የሚለው ቡድኑ ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያኖች ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ወግነው መንግስትን እንደተቃወሙ አድርጎ ያቀረበው የውሸት ድርደራ ነው፡፡ እርግጥ ነው ኢትዮጵያዊያን በእምነት፣ ቋንቋ፣ በብሔር ሳይገደቡ ይደጋገፋሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ በዳይና ተበዳይ ባለመኖሩ አንዱ ለአንዱ በመወገን በመንግስት ላይ የሚዘምትበት ሁኔታ የለም፡፡

ቡድኑ አሜሪካ ውስጥ ቁጭ ብለው ሳያዩ የባጥ የቆጡን የሚዘላብዱትን እነ አሸባሪውን ዶክተር ብርሃኑ ነጋን በዋቢነት ከመጠቀም ሀገራችን ውስጥ ያለውን ሃቅ ቢያይ በጀ ነበር። ግና ፍላጎቱ ኢትዩጵያ ውስጥ በህቡዕ ሁከት ማዘጋጀት በመሆኑ ይህንን ሊፈፅም አይፈልግም—ምንም እንኳን ሃሳቡ “ላም አለኝ በሰማይ…” እንዲሉት ዓይነት ቢሆንም።

ሌላው ቀርቶ በሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ የቡድኑ ምልከታ እርስ በርሱ የሚጣረስ ነው፡፡ በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊን በሃይማኖት ጉዳይ መለያየታቸውን ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዱ ከሌላኛው ጋር በመወገን መንግስትን እየተቃወመ እንደሆነ ያትታል፡፡ የሚጋጩ ተራ አሉባልታዎች ናቸው፡፡

የቡድኑ በሬ ወለደ ውንጀላ ተራ አሉባልታ ይመስለኛል። በእርግጥ ስለ እኛ እንደ እኛ ስለማይጨነቅና የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳዩ ባለመሆኑ ከፀረ - ኢትዮጵያን ጋር ተሰልፎ ያሻውንና የመሰለውን ድሪቶ ቢደርት መብቱ ነው፡፡ ሃቁን የምናውቀው እኛ ብቻ ነን፡፡

እኛ የምንፈልገው የሚያወሩብንን ሳይሆን የሚሰሩልንን ነው፡፡ በተግባር ሰርቶ ያሳየን ደግሞ ባህር ማዶ ተቀምጠው የሚያሚርቱ ቅምጥል ፖለቲከኞቻችንና አጫፋሪዎቻቸው እንዲሁም ግጭትን አስወግዳለሁ ባይ ቡድኑ ሳይሆኑ የኢትዩጵያ ህዝብና ኢህአዴግ ብቻ ናቸው፡፡

እናም ኢህአዴግ ማለት ደግሞ አቶ መለስ ማለት ብቻ አደለም፡፡ አህአዴግ አንድም ሚሊዮኖችም ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያዊያን ሆኗል፡፡ እልፍ አዕላፍ መለሶችንም አፍርቷል፡፡ እናም የአቶ መለስን ዕረፍት ተከትሎ ኢትዮጵያ ትበታተናለች እያሉ መጠንቆል የተሳሳተ ብርሃኑ ነጋዊና አክራሪ ኒዮ-ሊበራላዊ የከሰረ የፖለቲካ ስሌት ይመስለኛል፡፡ እናንተዬ ቀለምና ወረቀት አገኘሁ ብሎ ይህን ሁሉ የአሉባልታ ጋጋታ የሚያትተው ዓለም አቀፍ ቡድን ነኝ ባዩ “ድርጅት” እውን ግጭት አስወጋጅ ነው ወይስ ህቡዕ የሁከት አዘጋጅ?- እርግጥ የዚህ ጥያቄ ምላሽ የቡድኑና የውሸት ክምር ወሬ አቀባዩቹ ቢሆንም፤እኔ ግን ለዛሬው በዚሁ ላብቃ፡፡